**አንድ ተማሪ ቋንቋው የአፍ መፍቻው/ዋ ሳይሆን/ሳትሆን ነገር ግን ችሎታው/ዋ ከፍተኛ ከሆነ መሳተፍ ይችላል/ትችላለችን?**
አዎ፤ ነገር ግን ተማሪው/ዋ ፈተና የሚሰጥበትን ቋንቋ በኖቪስ መካከለኛ ደረጃ (Novice Mid) ወይም ከዚያ በላይ ማንበብ፣ መጻፍ፣ መናገር እና መስማት መቻል ይኖርበታል/ባታል። እባክዎን የግል መገምገሚያ ሰንጠረዥን ይመልከቱ። ተማሪዎቹ ሁሉንም ስራ በራሳቸው ማጠናቀቅ መቻል ይኖርባቸዋል።

**ፈተናው የሚሰጠው መቼ ነው?**
ፈተናዎች የሚሰጡት ኖቬምበር 5 (የምርጫ ቀን በመሆኑ ት/ቤቶች ዝግ ናቸው) በ Wakefield High School ነው።። **አንድ ዋነኛ የፈተና ቀን ብቻ ይኖራል። ለመመረቅ ክሬዲት የሚያስፈልጋቸው ሲኒየሮች በፀደይ ወቅት ለሚፈጠሩ ዕድሎች ከWorld Languages Office ጋር መነጋገር አለባቸው።።**

**ተማሪዎች የሚመዘገቡት እንዴት ነው?**
ተማሪዎች በኦንላይን ላይ በሚከተለው አድራሻ መመዝገብ ይችላሉ፦ **https://www.apsva.us/world-languages/credit-by-exam/**
ከዚያ በኋላ፣ ተማሪዎች የመፈተኛ ቀኑን፣ ሰዓቱን እና ቦታውን እንዲያረጋግጡ ይደረጋል።

**ምዝገባ ቀናት፡** ሴፕቴምበር 3 – አክቶበር 4፡

**መፈተን የሚቻሉት ቋንቋዎች ምንድን ናቸው?**
የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን ጨምሮ አብዛኛዎቹ ቋንቋዎችን ማግኘት ይቻላል። ለትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ እስከ 2 ክሬዲቶች የሚያስገኘውን የ FCPS ፈተና እንጠቀማለን። እባክዎ ያስተውሉ፡ በሚከተሉት ቋንቋዎች ፈተና ለመስጠት **እንደማንችል** ስንገልጽ እናዝናለን፡ ፉልዱድ፣ ካናዳ፣ ማላጋሲ፣ ማም እና ዞሳ።። ለሚፈጠረው አስቸጋሪ ሁኔታ ይቅርታ እንጠይቃለን።።

በድጋሚ የሚወሰዱ ፈተናዎች በተማሪው ወጪ ሲሆኑ ክፍያውም እንደየፈተናው ይለያያል።

**የፈተናው ውጤት የሚሰጠው እንዴት ነው?**
የፈተናው ውጤት የሚሰጠው በኮምፒውተር ወይም ፈተናው በተሰጠበት ቋንቋ ተናጋሪ በሆነ ገምጋሚ ይሆናል። ውጤቶቹም የመጨረሻ ናቸው እናም መልሶ ይታይልኝ ማለት አይቻልም። የሚሰጠው ክሬዲት በሚከተለው መሰረት ነው፦

**ተማሪዎች ፈተናውን በማለፋቸው ውጤት ይያዝላቸዋል?**
ተማሪዎች ፈተናውን ካለፉ፣ ለተመጣጣኙ ኮርስ "አልፏል"

| የብቃት ደረጃ | የተሰጠ ክሬዲት (ቶች) | ቀጣይ ምደባ | ቀጣይ SFS ምደባ |
|---|---|---|---|
| Novice High (ከፍተኛ ጀማሪ) | 1.0 | ደረጃ II | SFS II |
| Intermediate Low (ዝቅተኛ አማካይ) | 2.0 | ደረጃ III | SFS II |
| Intermediate Mid (መካከለኛ አማካይ) | 3.0 | ደረጃ IV | SFS III |
| Intermediate High (ከፍተኛ አማካይ) | 4.0 | ደረጃ V (A.P አይመከርም) | ደረጃ V (A.P አይመከርም) |

የሚል ውጤት የሚያገኙ ሲሆን ትራንስክሪፕታቸው ተገቢዎቹን ደረጃዎች በሚገባ ማሟላታቸውን የሚያሳይ "P" ይጻፋል። ተማሪዎች የአማካይ ውጤት ነጥባቸው (GPA) ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ምንም የውጤት ነጥብ አይሰጣቸውም።

**ውጤቶች የሚገለጹት እንዴት ነው?**
ወላጆች እስከ ጃንዋሪ ባለው ጊዜ ውጤቶቹን በደብዳቤ አማካይነት እንዲያውቁ ይደረጋሉ።

**ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የሚቻለው ከየት ነው?**
ለWorld Languages Office በስልክ ቁጥር 703.228.6097 ይደውሉ ወይም የትምህርት ቤት አማካሪ ጋር ይነጋገሩ።

# ክሬዲት-በ-ፈተና እና የሁለት ቋንቋ ተናጋሪነት

## 2019-20

World Languages Office

2110 Washington Blvd.
Arlington VA 22204

የስልክ ቁጥር፦ 703.228.6097
apsva.us/worldlanguages



Arlington Public Schools



**በፈተና-ውጤት- ክሬዲት ማግኘት (Credit-by-Exam) ምንድን ነው?**
የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች (APS) ከእንግሊዝኛ ሌላ ሌሎች ቋንቋዎች የመግባባት እና የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በተመረጡ የዓለም ቋንቋ ፈተናዎች በኩል የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲቶች እንዲያገኙ ይፈቅዳል። በፈተና-ውጤት- ክሬዲት ማግኘት (Credit-by-Exam) የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አራት የውጭ ቋንቋ ክሬዲቶችን ለመስጠት የተማሪዎችን የውጭ ቋንቋ ብቃት ይመዝናል። በሃገር ደረጃ በታወቁ እንደ STAMP፣ AAPPL እና OPI የመሳሰሉ ፈተናዎች እንዲሁም ለአብዛኞቹ ቋንቋዎች ደግሞ WPTን እንጠቀማለን።

**በፈተና-ውጤት-ክሬዲት ማግኘት (Credit-by-Exam) ላይ ተሳትፎ ማድረግ እንዴት ነው ተማሪዎችን የሚያግዘው?**
ተማሪዎች በላቁ ትምህርቶች ዲፕሎማ Advanced Studies Diploma (ASD) መመረቅ ከፈለጉ በዓለም ቋንቋ ክሬዲቶች ማግኘት ያስፈልጋቸዋል። እነዚህም የሚገኙት ለሶስት ዓመታት/ክሬዲቶች አንድ ቋንቋ (3 x 1) ወይም ሁለት ዓመታት/ክሬዲቶች ሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች (2 x 2) በመውሰድ ነው።

**በፈተናው ስንት የዓለም ቋንቋ ክሬዲቶች ማግኘት ይቻላል?**
ተማሪዎች በፈተናው ባሳዩት የብቃት ደረጃቸው መሰረት እስከ አራት ክሬዲቶች ወይም እንደ ፈተናው ዓይነት ሁለት ክሬዲቶች ድረስ ማግኘት ይችላሉ። አንድ ተማሪ በቋንቋ ክህሎቱ ምክንያት ወደ ደረጃ III ወይም IV ክፍል ከተመደበ፤ ለቀድሞ ደረጃዎች ወደኋላ ተመልሶ ክሬዲት ለማስያዝ ፈተና መውሰድ ይችላል። አንድ ተማሪ በደረጃ III ላይ እየተማረ ከሆነና በፈተናው ላይ 4 ክሬዲቶች ካገኘ ትራንስክሪፕቱ ላይ የሚጨመረው አንድ ክሬዲት ብቻ ነው። **ለተመሳሳይ የዓለም ቋንቋ ኮርስ ከአንድ በላይ ክሬዲት አይሰጥም።**



**በዚህ ፈተና የተገኘ ውጤት ተማሪዎች የ Seal of Biliteracy (ሲል ኦፍ ባይሊትረሲ) ሽልማት እንዲያገኙ የሚረዳቸው እንዴት ነው?**
ከ2015-16 ጀምሮ የትምህርት ቦርድ Seal of Biliteracy የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመራቂዎችን ከእንግሊዝኛ በተጨማሪ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ቋንቋ የከፍተኛ ችሎታ ደረጃ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል። ሁሉንም የሚያስፈልጉ የኮርስ መጨረሻ መመዘኛ ፈተናዎች በእንግሊዚኛ አጥጋቢ ወይም ከፍተኛ ደረጃ ላመጡ (የ11ኛ ክፍል SOL) እንዲሁም በሌላ ቋንቋ በአገር ደረጃ በታወቀ ፈተና መካከለኛ-አማካይ ደረጃ ወይም ከፍተኛ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች የSeal of Biliteracy ሽልማት ይሰጣቸዋል። Seal of Biliteracy ሽልማት ይሰጣል እንዲሁም በተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ላይ ይደረጋል።

**ፈተናውን ለመፈተን ብቁ የሚሆነው ማን ነው? ተማሪዎችስ ለዚህ ፈተና ብቁ መሆናቸውን እንዴት ነው የሚያውቁት?**
ከ7ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ብቁ ብቁ ሊሆኑ የሚችሉት፣ ቢያንስ በኖቪስ ሚድ (Novice Mid) ደረጃ መሆን እና የሚከተሉትን መቻል አለባቸው፦

- ቀላል ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ።
- በውይይት ውስጥ ለሌላ ሰው ምላሽ በመስጠት ቀላል አረፍተ ነገሮችን መስራት
- መሰረታዊ መረጃዎችን ማስተላለፍ።
- መውደድን እና መጥላትን መግለጽ።
- መሰረታዊ ቅጽን መሙላት።
- የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ዝርዝር ማንበብ እና መጻፍ።

እባክዎ በሚከተለው አድራሻ ላይ የሚገኘውን የግለ ምዘና ሰንጠረዥ ይመልከቱ፡
http://www.apsva.us/worldlanguages

**ESOL/HILT A እና B** በማግኘት ላይ ያሉ ተማሪ ከሆኑ፣ እነዚህን አገልግሎቶች እያገኙ መሆንዎትን በምዝገባ ቅጽ ላይ መጥቀስዎን ያረጋግጡ፤ እኛም ሌላ ፈተና መውሰድዎን እናረጋግጣለን።

**ፈተናውን መውሰድ የሌለበት ማን ነው?**

- በአሁኑ ወቅት በደረጃ IV ወይም SFS III ክፍል የተመዘገቡ ተማሪዎች ፈተናው በፀደይ ወቅት ይሰጣቸዋል።
- ከአሁን በፊት በነበረ የዓለም ቋንቋ ኮርስ የተገኘ ውጤታቸውን ማሻሻል የሚፈልጉ ተማሪዎች።

**ምን ያህል ያስከፍላል?**
ለአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ተማሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ምንም ክፍያ አያስከፍልም።